የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No.37
ADDIS ABABA 30th March..2004

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፯/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ከአልጄርያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ......................ገጽ ፪ሺ፮፻፲፩

## CONTENTS

Proclamation No. 397/2004

The Agreement on Promotion and Reciprocal Protection of Investment with the Peoples Democratic Republic of Algeria Ratification Proclamation No........................ Page 2611

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፯/፲፱፻፺፮

### የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከአልጄርያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት ያደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በአልጄርያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የሚያስችል ስምምነት ግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገሮች ሕጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ በመገለፁ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

## PROCLAMATION NO. 397/2004.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND AHT GOVERNMENT OF THE PEOPLE'S DEMOCRATIC REPUBLIC OF ALGERIA ON THERECIPROCAL RPOMOTION AND PROTECTION OF INVESTMENTS

**WHEREAS,** the Agreement of the Reciprocal Promotion and Protection of Investments between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the People's Democratic Republic of Algeria is signed in Addis Ababa, on May 27,2002;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel;

**WHEREAS,** the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 30th day of March, 2004;

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል::

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ከአልጄርያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፯/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአልጄርያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ፣ ግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል::

**፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኃላፊነት**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል::

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "The Agreement on Promotion and Reciprocal Protection of Investment with the Peoples Democratic Republic of Algeria Ratification Proclamation No. 397/2004."

**2. Ratification of the Treaty**

The Agreement on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment signed in Addis Ababa on May 27, 2002 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the People's Democratic Republic of Algeria is Ratified.

**3. Responsibility of the Ethiopian Investment commission**

The Ethiopian Investment commission is hereby empowered to implement this Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as of 30th day of March, 2004

**Done at Addis Ababa, this 30th day of March, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት